# “መሬት ለአራሹ” - ለኢትዮጵያ የዳቦ ቅርጫትነት ትንሳዔ!

(ከአብዱራህማን አህመዲን፤ የቀድሞ የፓርላማ አባል)
Email: ahayder2000@gmail.com

*(ይህ ጽሑፍ ዛሬ መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ.ም በወጣው ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ታትሟል፡፡ ጋዜጣውን ያላገኙ ሰዎች ቢያነቡት ይጠቅማል፣ መወያያም ይሆናል በሚል መንፈስ በዚህ ድረ-ገጽ ላይ እንዲታተም ተልኳል)*

በአዲስ አበባ ከተማ፣ በምኖርበት አያት - መሪ አካባቢ አንዲት አነስተኛ ባህላዊ ገበያ አለች፡፡ የአካባቢው አርሶ አደሮች በየሳምንቱ ረቡዕ እና ቅዳሜ ወደዚች ገበያ ምርታቸውን ይዘው በመምጣት ከከተሜው ህብረተሰብ ጋር ይገበያያሉ፡፡ ባለፈው ረቡዕ እለት ከመሪ ወደ አያት - ኮንዶሚኒየም ለመሄድ ታክሲ ውስጥ ስገባ ዘንቢልና ሌሎች ነገሮችን ያንጠለጠሉ አንዲት እናት ተከትለውኝ ገቡ፡፡ የያዙትን እቃ ተቀበልኳቸውና ከጎኔ ተቀመጡ፡፡

“ዘላለም ለማይሞላ ጉድጓድ...” አሉ የመማረርና የመሰላቸት ቃና ባለው ድምፀት፡፡ “ምንድነው እሱ እማማ” አልኳቸው፡፡ “ሆዳችን ልጄ! ዘላለም የማይሞላ ጉድጓድ! እሱን ለመሙላት እድሜ ልክ መመናተል!... እዳ ነው እቴ!... ኤዳልኝ!...” አሉ ምርር ብለው፡፡ “ከገበያ ነው የመጡት?” አልኳቸው፡፡ “አዎ!...” አሉኝ፡፡ ቀጠልኩና “እንዴት ነው ገበያው ታዲያ?” በማለት ጠየቅኳቸው፡፡ “ምን እንዴት አለው ልጄ!... ዱሮ ሃያ ብር ይዘን መርካቶ ከሄድን የምንፈልገውን አስቤዛ ገዝተን እንመለስ ነበር... ‘ማሪኝ እናት መርካቶ!’ ያስብላል፡፡ ዛሬ ሃያ ብር መርካቶ አድርሶ አይመልስህም፡፡ በዚያ ላይ... ያልተወደደ ምን ነገር አለ?! ሦስት መቶ አራት መቶ ብር ይዘህ ወጥተህ ለሳምንት የሚሆን አስቤዛ መግዛት አትችልም፡፡ ቃሪያ በአቅሟ በመደብ በመደብ መሸጧ ቀርቶ እንደ ከረሜላ በቁጥር ሆኗል፡፡ ያውም የሞተ ቃሪያ!...” ንግግራቸውን ቆም አድርገው በመስኮት አሻግረው ይመለከቱ ጀመር...፡፡

ታክሲው ውስጥ የተከፈተውን ሬዲዮ እየሰማን ዝም ዝም ተባባልን፡፡ በሬዲዮ የገበያ ዋጋ መረጃ እየቀረበ ነበር፡፡ በሬዲዮው መልእክት ፈገግ አሉና “ሁሉም ነገር ርካሽ የሆነው የት እንደሆነ ታውቃለህ?...” አሉና የእኔን መልስ ሳይጠብቁ ንግግራቸውን ቀጠሉ “ሁሉም ነገር ርካሽ የሆነው ኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ውስጥ ነው” አሉ፡፡ ታክሲው ውስጥ የነበረው ሰው ሁሉ ከት ብሎ ሳቀ፡፡ “ውነቴን እኮ ነው!... አትሳቁ!... ጋዜጠኞቹ ገበያ ገብተው የሚያውቁ አይመስለኝም” ሲሉ አሁንም ታክሲው ውስጥ ያለው ሰው በሳቅ አውካካ፡፡ ሁሉም በሆዱ የሚያብሰለስለውን ሴትዮዋ ስለተናገሩት የምሬት ሳቅ እንደሳቁ ያስታውቃል፡፡

ይህንን ሃሳብ የዚች መጣጥፌ መነሻ ያደረግኩት ያለምክንያት አደለም፡፡ በሀገሪቱ ያለው የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ሰውን እያማረረ ነው፡፡ መማረር ብቻም አደለም፡፡ በተለይ እዚህ አዲስ አበባ በሚያገኙት ገቢ መኖር ስላልቻሉ ሰዎች ለልመና እየተዳረጉ መሆኑም እየተስተዋለ ነው፡፡ ይህንን አባባሌን ለማረጋገጥ ሁለት ማሳሌዎችን ልጥቀስ፡፡ ባለፈው ሰሞን ያጋጠመኝ ነው፡፡ ከካዛንቺስ ወደ ኡራኤል ለመሄድ ሰዎች ተራ ይዘው ታክሲ ይጠብቃሉ፡፡ እኔም የሰልፉ መጨረሻ ላይ ጠጋ ብየ ቆምኩ፡፡ ታክሲው እስኪመጣ በመጠባበቅ ላይ እንዳለን በርካታ እድሜአቸው ጠና ያሉ አረጋውያን (ሴትም ወንድም) የተለያዩ መላእክትንና የፈጣሪን ስም እየጠሩ ይለምናሉ...

ከሁሉ ከሁሉ የእኔን ቀልብ የሳቡት አንዲት እናት ናቸው፡፡ ያማረ የሀበሻ ጥበብ ቀሚስ ለብሰዋል፡፡ ጥሩ የሚባል ጫማም ተጫምተዋል፡፡ ጥሩ የቤት እመቤት መሆናቸው ያስታውቃል፡፡ መጀመሪያ ላይ ልመና ላይ የተሰማሩ አልመሰለኝም ነበር፡፡ የሆነ ስለት ደርሶላቸው ቃል የገቡትን ስለት ለማድረስ የሚለምኑ ነበር የመሰለኝ፡፡ ነገሩ የገባኝ እኔ አጠገብ ደርሰው “ወንድሞቼ፣ እህቶቼ፣ ልጆቼ፣... እሰው ፊት እንደ መቆም ከባድም መጥፎም ነገር የለም፡፡ በኔ የደረሰው አይድረስባችሁ፡፡ እናንተ ፊት የቆምኩት ወድጄ አደለም፡፡ ... ዱሮ እሰው ቤትም ተቀጥሬ እሰራ ነበር፡፡ አሁን ደከምኩ፡፡ እንጀራ መጋገር እንኳ አልቻልኩም፡፡ የባሌ ጡረታ ለቤት ኪራይ እንኳ መሆን አልቻለም፡፡ እንዴት ልሁን...” እያሉ እንባቸውን ሲያወርዱት ያየ ሁሉ በሀዘኔታ እጁን ዘረጋ...፡፡

ይህን ሁኔታ በውስጤ እያብሰለሰልኩ ታክሲው መጥቶ ተሳፍሬ ኡራኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ወረድኩ፡፡ … እዚያም ጉዳዬን ጨርሼ እንደገና ታክሲ ለመያዝ ሳዘግም አንዲት እናት ነጠላቸውን በእጃቸው ለልመና ዘርግተው “ልጆቼ ከፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ነው የመጣሁት፡፡ የቤት ኪራይ 150 ብር መክፈል አቅቶኝ…” አሉ፡፡ አሁንም ልመና! መገናኛ እና ገርጂ አካባቢም እንዲሁ ተመሳሳይ ልመና አጋጥሞኛል፡፡ በርግጥ የአዲስ አበባ ነገር አስቸጋሪ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቷ አቀራረብ የአንድ ሰሞን የገንዘብ ማግኛ ዘዴ ልትሆን ትችላለች፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን በውስጧ አንዳች እውነታ ሊኖር እንደሚችል አስባለሁ፡፡ የኑሮ ውድነቱ ሰውን ለልመና ከቤቱ እያስወጣው አደለም ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ነው፡፡

በርግጥ ዱሮና ዘንድሮ አንድና ያው ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ምንም ነገር ዱሮ በነበረበት ሁኔታ፣ መጠን፣ ዋጋ፣… ዘንድሮ ሊገኝ አይችልም፡፡ በነፃ የምንተነፍሰው አየር እንኳ የዱሮውና የዘንድሮው አንድ አደለም፡፡ የዘንድሮው አየር በፋብሪካ ጭስ የተበከለ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ እናም ዛሬ ዛሬ ከፊል አየር፣ ከፊል የፋብሪካ ጭስ ስለምንተነፍስ እንደ ሞተር የማጓራት ዓይነት ባህሪ ሊታይብን ይችላል፡፡ ብቻ ለዚሁም “ክፈሉ” እንዳንባል በጣም በጠሎት መትጋት ሳይኖርብን አይቀርም!

በሀገራችን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ዋጋ ንሯል፡፡ ኑሮ ጣሪያ አልፎ ሰማይ ነክቷል፡፡ በደመወዝ የሚኖረው ከተሜ ደመወዙና ኑሮው አልተመጣጠኑም፡፡ በተለይ የቤት ኪራይ የሚቀመስ አልሆነም፡፡ ኢኮኖሚስቶች አንድ ሰው ከደመወዙ ላይ ለቤት ኪራይ እስከ 35% መመደብ እንደሚኖርበት ይናገራሉ፡፡ በእኛ ሀገር ግን በአሁኑ ወቅት የአንድ ሰው ደመወዝ ሙሉ ለሙሉ ለቤት ኪራይ ቢመደብም በቂ ሊሆን አልቻለም፡፡ የመንግስት ሠራተኛው “በአስማት ነው የሚኖረው” የሚለው አባባል ከቀልድነቱ በላይ ብዙ መልእክት የሚያስተላልፍ ይመስለኛል፡፡

ፓርላማ እያለሁ አንዳንድ የፓርላማ አባላት የወር ደመወዛቸው አልበቃቸው እያለ በመኖሪያ አካባቢያቸው ካሉ ሱቆች ዱቄት በብድር ይወስዱ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ የጎረቤታችን የኬንያ ፓርላማ አባላት ግን መንግስት ዓመታዊ በጀት ይዞ ሲቀርብ የመጀመሪያ ጥያቄቸው ‘የእኛስ ደመወዝ ጨምሯል?’ የሚል ነው አሉ፡፡ ደመወዝ ሳያስጨምሩ በጀት አያጸድቁም፡፡ የእኛ አገር ውሻ ሉኳንዳ ቤት በር ላይ ጅራቱን እየቆላ፣ ዓይኑን እያቁለጨለጨ አርፎ እንደሚቀመጠው ሁሉ፤ ፓርላማችንም ‘ጨዋ’ ነው፡፡ ያገሩን መንግስት አያስጨንቅም፡፡

ደግነቱ ለፓርላማ አባላት የመንግስት ቤት ስለሚሰጣቸውና የቤት ኪራዩ ቢበዛ ከ400 ብር በላይ ስላልሆነ ነው እንጂ የመንግስታችንን አንገት ለማነቅ ግብግቡ የሚጀምረው ፓርላማ ውስጥ መሆኑ ጥርጥር አልነበረው፡፡ ያም ሆኖ አንዳንዶቹ የፓርላማ አባላት ከመኖሪያ ቤታቸው ላይ አንድ ወይም ሁለት ክፍል (እንደ ቤታቸው ስፋት) ቀንሰው (የኢህአዴግም የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ጭምር) ያከራዩ ነበር፡፡ መቼም “ምቀኛ” አይጠፋም፣ ይህንንም እንዳያደርጉ “የተከራዩ ማንነት ስለማይታወቅ ለምክር ቤት አባላቱ ደህንነት አስጊ ነው” በሚል ሰበብ ኮሚቴ ተቋቁሞ ቤት የሚያከራዩ የፓርላማ ቤት አባላት ተለይተው ታውቀው እርምጃ እንዲወሰድ እንቅስቃሴ መደረጉን አስታውሳለሁ፡፡

ፓርላማው የግዝፈቱን ያህል የሚጻፍለትም፣ የሚጻፍበትም ብዙ ነገር አለው፡፡ ለጊዜው እሱን እንተወውና ወደ ኑሮ ውድነቱ እንመለስ፡፡ የኑሮ ውድነቱን እንዲህ ያናረው ምንድነው? የሚል ጥያቄ ሲነሳ፤ ኢህአዴግ “የኢኮኖሚ እድገቱ ራሱ የፈጠረው ነው” የሚለውን ጨምሮ በርካታ ምክንያቶችን ይደረድራል፡፡ በርግጥ “የኢኮኖሚ እድገት የኑሮ ውድነትም ሆነ የዋጋ ንረት አያመጣም” ብሎ መከራከር የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ብቸኛም ባይሆን አንዱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡

በመንግስት በኩል በተከፈቱ የኮብል ስቶንም ይሁን፣ የኮንዶሚኒየም ቤት ግንባታ አሊያም የመንገድና የባቡር ሐዲድ ዝርጋታ ስራዎች ምክንያት ዜጎች ስራም ገቢም ማግኘታቸው ይታያል፡፡ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅቶ መስራትም ወፍራም ገቢ እያስገኘ ነው፡፡ ቀድሞ ከአንድ ቤት ገቢ የሚያገኘው አንድ ሰው ነበር፡፡ አሁን አሁን ከአንድ ቤተሰብ ገቢ የሚያገኘው ሦስት አራት ሰው ሲሆን፤ ገቢ ጨመረ ማለት ነው፡፡ ገቢ ሲጨምር ፍላጎት (Demand) መጨመሩም ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ፍላጎት ሲጨምር አቅርቦት (Supply) በቂ አይሆንም፡፡ የአቅርቦት በቂ አለመሆን ደግሞ ዋጋ ማናሩ የሚጠበቅ ነው፡፡

እዚህ ላይ “አቅርቦት በቂ ያልሆነው ለምድነው?” የሚል ጥያቄ አንስቶ ምላሽ ለመስጠት መሞከር ተገቢ ይመስለኛል፡፡ የተትረፈረፈ ምርት አለማምረት ለግብርና ምርት አቅርቦት ማነስ ዋነኛው ምክንያት መሆኑ ይታመናል፡፡ የተትረፈረፈ የጤፍ

ምርት፣ የተትረፈረፈ የማሽላ፣ የስንዴ፣ የገብስ፣ የበቆሎ፣ የሸንኩርት፣ የድንች፣ ወዘተረፈ ምርት ከተመረተ የተሟላ አቅርቦት ይኖራል፡፡ እናም ሸማቹ ዋጋ ተደራዳሪና ወሳኝ ኃይል መሆን ይችላል፡፡ አምራቹም የሚያዋጣው ሀቀኛ ዋጋ (Reasonable Price) ላይ ይቆማል፡፡ “ደላላ መር” አርቲፊሻል ዋጋ ቁለላ እድል ያጣል ማለት ነው፡፡

ሌላው መነሳት የሚገባው ቀጣይ ጥያቄ *“ታዲያ የተትረፈረፈ ምርት ለማምረት ችግሩ ምንድነው?”* የሚል ይሆናል፡፡ ችግሩ ብዙ ምርምር የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ አጭርና ግልጽ ይመስለኛል፡፡ ችግሩ **መሬት** ነው፡፡ አሁን ያለው የአርሶ አደሩ መሬት የበሬ ግንባር የምታህል ናት፡፡ እሷም ለዘመናት ስትታረስ የኖረች፣ የማምረት አቅሟ የነጠፈ ነው፡፡ እናም የነጠፈና የበሬ ግንባር የሚያህል መሬት በማረስ የተትረፈረፈ ምርት ሊገኝ አይቻልም፡፡ ይህም በመሆኑ አርሶ አደሩ እንኳን የተትረፈረፈ ምርት አምርቶ የገበያ ፍላጎትን ሊያሟላ ቀርቶ ራሱን መመገብ እያቃተው ልጆቹን ወደ ዐረብ ሀገራት የመላክ አማራጭ ውስጥ ገብቷል፡፡

ዛሬ ከተሜውም ይሁን ገጠሬው በእቁብም፣ በብድርም እየኖረ ሊሆን ይችላል፡፡ ከስደት በሚገኝ ገቢ (Remittance) እየኖረም ሊሆን ይችላል፡፡ በትርፍ ጊዜ ከተሜው በድለላ፤ ገጠሬው በቀን ስራ ከሚያገኘው ገቢ ቤቱን እየደጎመ ሊሆን ይችላል፡፡ አነስተኛ የቤት ኪራይ ፍለጋ ወደ ከተሞች ጠርዝ ወጥቶ መኖር አማራጭ የኑሮ መፍትሄ ተደርጎም ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላም ሌላም አማራጮች እየተሞከሩ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ ግን ዘላቂ መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል ሁላችንም የምንገነዘበው ይመስለኛል፡፡

መንግስት በዚህ ወቅት ግሽበቱ የቀነሰ ወይም ባለበት የረጋ መሆኑን ይናገራል፡፡ በበኩሌ እንዲህ ያለው ሁኔታ ሊስተዋል የቻለው በሁለት ምክንያቶች መሆኑን እገምታለሁ፡፡ አንደኛ፤ መንግስት በከተሞች አካባቢ ያለውን የግንባታና ሌሎች ሥራዎች በተወሰነ ደረጃ ስለገታ ወይም መጠኑን ስለቀነሰ ወይም አዳዲስ ፕሮጀክቶች እስከሚጀመሩ ድረስ በተፈጠረው ክፍተት ምክንያት ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት በተለይም በአዲስ አበባ ዜጎች በተለያዩ የኮንዶሚኒየም ቤት ግንባታ ፕሮግራሞች ገንዘብ በባንክ እንዲቆጥቡ በመደረጉ ወደ ገበያ የሚወጣው የብር መጠን በተወሰነ ደረጃ በመቀነሱ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

በርግጥ ህብረተሰቡ ወደ ቁጠባ የሚወስደው ብር ተጨማሪ ወጪዎቹን በማቆም እንጂ መደበኛ ፍጆታዎቹን (ቀለቡን) በመቀነስ ሊሆን እንደማይችል ይታመናል፡፡ እናም እነዚህ ዋጋን ያረጋጉ የሚመስሉ ሁኔታዎች ዘላቂነት ያላቸው መፍትሄዎች ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም፡፡ እናስ መፍትሄው ምንድነው? ያልን እንደሆነ፤ በእኔ በኩል አንድ መፍትሄ ይታየኛል፡፡ ይኸውም፤ የተትረፈረፈ ምርት ለማምረት ብቸኛው መፍትሄ ለአርሶ አደሩ ተጨማሪ የእርሻ መሬት ማዘጋጀት ነው፡፡

*“ተጨማሪ መሬት ከየት ይገኛል?”* ለሚለው ቀጣይ ጥያቄ በበኩሌ ሁለት አማራጮች ይታዩኛል፡፡ አንደኛ፤ በደርግ ስርዓት *“የመንግስት እርሻ” ተብለው የተያዙና* እስከ አሁን ድረስ በመንግስት ይዞታነት የሚታወቁ መሬቶች ናቸው፡፡ እነዚህ መሬቶች በብዙ ክልሎች የሚገኙ ሲሆን፤ በአንዳንዶቹ የጎመን ዘር እየተመረተባቸው መሆኑን በዓይኔ በብረቱ አይቻለሁ፡፡ አንዳንዶቹን ደግሞ ዳዋ በልቷቸው፣ የተዘረጉት መሰረተ ልማቶች ተበለሻሽተው ተመልክቻለሁ፡፡ ስለሆነም፤ እነዚህን መሬቶች በአካባቢው ላሉ አርሶ አደሮች አከፋፍሎ በግል እንዲያርሷቸው ማድረግ ወይም በማህበር እየተደራጁ የህብረት እርሻ (union) እንዲመሰርቱ በማድረግ ማከፋፈል አስፈላጊ ነው፡፡

የመሬት ክፍፍሉ ከተካሄደ በኋላ በግብርና ሚኒስቴር አማካይነት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አስተማማኝ ሀገራዊ የተትረፈረፈ ምርት እንዲመረት ማድረግ ቀጣይ ስራ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው አማራጭ በየክልሉ ለኢንቨስትመንት ተብለው ከተያዙ መሬቶች ውስጥ የተወሰነውን ቀንሶ በአካባቢው ያሉ መሬት አልባ ወጣቶች በማህበር ወይም በግላቸው እንዲያርሱት ማከፋፈል ነው፡፡ የዚህንም ሂደት በግብርና ሚኒስቴር አማካይነት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

መንግስት እነዚህንና ሌሎች ተጨማሪ የመፍትሄ ሃሳቦችን በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚወስድ ካልሆነ በስተቀር የኑሮ ውድነቱም ሆነ የዋጋ ንረቱ የሚገታ አይሆንም፡፡ እንዲያውም በቀጣይ ጊዜአት አርሶ አደሩ ከራሱና ከቤተሰቡ ቀለብ ተርፎት ወደ ገበያ የሚያወጣው ትርፍ ምርት ስለማይኖረው ገበያ ላይ በኪሎ ቀርቶ በስኒ የሚሸመት እህል ማግኘት የሚቻል ሆኖ

አይታየኝም፡፡ ይህ ደግሞ ዶ/ር መራራ ጉዲና ደጋግመው እንደሚሉት የተራበ ሕዝብ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ መሪዎቹን “ማስቸገሩ” የሚቀር አይሆንም፡፡

መሬትን በሕዝብ ስም መንግስት እንዲያስተዳድር ከሚፈለግባቸው ምክንያቶች አንዱ ፈታኝ ሁኔታዎች ሲገጥሙ ሕዝብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ እርምጃዎችን ለመውሰድ እንዲችል እንጂ፤ መሬቶችን አጥሮ ማንም እንዳይነካቸውና በአጠገባቸው ዝር እንዳይል ለመጠበቅ አይመስለኝም፡፡ ሕዝባችንን በዚህ ወቅት ከገጠመው የባሰ ፈታኝ ሁኔታ ሊገጥመው እንደማይችልም አስባለሁ፡፡ ስለሆነም፤ መንግስት ለሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ለራሱም ህልውና ሲል አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡ እንደኔ እንደኔ በመጪው የምርት ዘመን በርካታ ጠፍ መሬቶች ለሕዝብ ተከፋፍለው እንዲታረሱ ቢደረግ፤ ለመንግስትም፣ ለከተሜውም ሆነ ለገጠሩ ሕዝብ በነፍስ መድረስ ሆኖ ይታየኛል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር ስር የአደጋ ዝግጁነት ፈንድ አቋቁሞ ሰዎች እስከሚራቡና ቀያቸውን ለቀው እስከሚሰደዱ ድረስ ከመጠበቅ ይልቅ ያንን ፈንድ በማህበር የተደራጁ ዜጎች በአነስተኛ ወለድ እንዲወስዱ ወይም እንደ ትራክተር ያሉ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችንና ምርጥ ዘር ጭምር በማቅረብ አስፈላጊውን ሀገራዊ ምርት እንዲያመርቱ ቢያደርግ አደጋን መከላከል ብቻ ሳይሆን፣ ማስወገድ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

መንግስታችን ለሕንዶች፣ ለዐረቦችና ለሌሎች ባለሀብቶች እርሻ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ መሬት በመስጠቱ ድርጊቱ “የመሬት ቅርምት” (Land Grab) ነው እየተባለ ይተቻል፡፡ እነዚያ ባለሀብቶች መሬቱን በወሰዱበት ወቅት ከራሳችን ቀለብ ተርፎ ለኢንቨስትመንት ጭምር የሚሆን ምርት እንደሚያመርቱ በሬዲዮም በቴሌቪዥንም ሲነገር ሰምተናል፡፡ ይሁን እንጂ ውጤቱ “ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ” ሆኖብናል፡፡ እንዲህ ያለው ውጤት አልባ ሁኔታ ደግሞ ዳር ላይ ሆነን ሁኔታውን ስንታዘብ የነበርነውን ጭምር “የመሬት ቅርምት (Land Grab) ነው” ወደሚሉት ወገኖች ጎራ እንድንቀላቀል እየገፋፋን ነው፡፡

እናም፤ እነዚያ ኢንቨስተሮች በአጭር ጊዜ ወደ ልማት ገብተው የምንፈልገውን ካላመጡልን ጫማቸው ላይ ያረፈቺውን አፈር እያራገፉ ወደ መጡበት በሰላም ቢሸኙና ከዚያ በኋላ፤ መሬቱም የኛው፣ ልማቱም የኛው፣ አልሚዎቹም እኛው፣… የምትል መፈክራችንን አስተጋብተንና በአጭር ታጥቀን እኛው ራሳችን ወደ እርሻ ልማቱ ብንሰማራ ይሻላል ባይ ነኝ፡፡ ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ያልታረሱ መሬቶች ማረስ ለሚችሉ የአዲሱ ትውልድ አርሶ አደሮች በግልም ይሁን በማህበር መከፋፈል ይኖርበታል፡፡

መሬት - ለአዲሱ አራሽ ትውልድ እንዲከፋፈል ከተደረገ የኢትዮጵያ የዳቦ ቅርጫትነት ትንሳዔ እውን መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ መንግሥት ምቹ ሁኔታዎችን ከፈጠረ በየከተማው ያለው ሥራ ፈላጊ አውደልዳ ሁሉ መተማም፣ ሁመራም፣ አሳኢታም፣ መልካ ዋከናም፣ ጭላሎም፣ ወላይታ ሰላም በርም፣ ጋምቤላም፣ ደገሐቡርና ጎዴም፣ ሐዋሳም ሆነ አሶሳ፣… ወርዶ ላቡን ለማፍሰስ ወደ ኋላ የሚል ሆኖ አይታየኝም፡፡ እምቢ ካለም አስገድዶም ቢሆን ሰርቶ እንዲበላ ማድረግ ጽድቅ እንደሆነ እንጂ ኩነኔ የለውም ባይ ነኝ፡፡

ለታላቁ አባይ ግድብ ብድርም እርዳታም ሳንሻ በራሳችን ሀብትና ጉልበት በመመካት ስራውን እንደጀመርን ሁሉ የሀገራችንን የዳቦ ቅርጫትነት ለመመለስም ራሳችን በራሳችን በንቅናቄ መልክ መነሳት አለብን፡፡ ተጨማሪ ግብዓት ሳያስፈልገው ታርሶ ውጤት ማምጣት የሚችል ድንግል መሬት እያለን፤ ማረስ፣ መዝራት፣ ማረም፣ ማጨድና መውቃት የሚችል ጉልበት እያለን በኑሮ ውድነት መንገላታት፣ በዋጋ ንረት መማቀቅ አለብን? የለብንም!